# ከሰው መርጦ ለሹመት ከእንጨት መርጦ ለታቦት

**_ዘመናዊ ቅድመ መጋባት ሥርዓተ ውይይት_**

በአዲስ አበባ ዘመናዊ ጋብቻ ከመፈጸሙ በፊት ሁለቱ ተጋቢዎች በተለያዩ ምክንያቶች ይተዋወቃሉ፥ ይፈቃቀዳሉ፥ ግብብነታቸው ሲበስል ለጋብቻ ይተጫጨጫሉ። በዚሁ መሠረት ከወንዱ ወገን ሰለ ቤተሰቡና ስለ ራሱ የሚያውቁ ዘመድና ጎረቤት ግለሰቦች ወደ ተገቢዋ ሴት ቤተሰብ ይላካሉ። ይኸውም በልጅቷ በተገቢዋ በኩል ወይም በሌላ አማካይነት የተወሰነ ቀን ሰዎች፥ እንግዶች እንደሚመጡ ለአግቢዋ ቤተሰብ ይነገራል። በተወሰነውም ቀን ከአግቢው ወገን ከሦስትና ከአራት ያላነሱ ሰዎች ለሽምግልና ወደ ተገቢዋ ቤተሰብ ይሄዳሉ። አባትና አንዳንዴም እናትን የጨመረና የታወቁ የቅርብ ዘመድ ሽማግሌዎች በቡድን ተቀምጠው ያግቢውን ቡድን ሽማግሌዎች ይጠብቃሉ።ያግቢው ቡድን ሽማግሌዎችም ተጠሪ ሆኖ የሚናገር ሰው መጀመሪያውኑ ሰይመው ስለሚሄዱ ወደ ቤተሱ ይገቡና የተሰየሙት የተገቢዋ ሴት ሽማግሌዎች ፊት ተደርድረው ይቆሙና እጅ ይነሳሉ። በዚሁ መሠረት ሃሳብ ይለዋወጣሉ።

| | |
|---|---|
| የወንዱ ቡድን ሽማግኬዎች | – "ጤና ይስጥልኝ" ይሉና ይቆማሉ። |
| የሴት ቡድን ሽማግሌዎች | – (ደጋግመው) ቁጭ በሉ ቁጭ በሉ ይላሉ። |
| የወንድ ቡድን ተጠሪ | – አንቀመጥም። የመጣንበትን ጉዳይ አስረድተን መልሱን ሳናገኝ ፥ ጉዳያችንን ቆመን እንድናስረዳ ይፈቀድልን። |
| የሴት ቡድን ሽማግሌዎች | – ተቀምጣችሁ ማስረዳት ትችላላችሁ እኮ! |
| የወንድ ቡድን ተጠሪ | – የመጣንበት ጉዳይ እጅግ ከፍተኛ ስለሆነ፥ ክብደት ያለው ስለሆነ ቆመን እንድናስረዳ ይፈቀድልን። |
| የወንድ ቡድን | – መቼም በዚህ ዓለም ልጆች ይወለዳሉ፥ ያድጋሉ፥ ለቁም ነገርም ሲደርሱም ወንድና ሴት ለትዳር እና ለጋብቻ ይፈላለጋሉ። ይህ ደግሞ ከሁሉም የበለጠና የተቀደሰ ተግባር መሆኑን ከእኛ የላቀ እናንተ ትረዳላችሁ። ታዲያ " ከሰው መርጦ ለሹመት፥ ከእንጨትም መርጦ ለታቦት" ይባላልና ፈቃዳችሁን በትህትና እንጠይቃለን። |
| የሴት ቡድን | – ለመሆኑ ብዙ ሴት ልጆች አሉንና ማንን ነው? |
| የወንድ ቡድን | – ሁለተኛ ልጃችሁን አስቴር ጃለታን ለልጃችን ለአፈወርቅ ዮሐንስ ነው። ወደ ፊት ትደርሱበታላችሁ። አፈወርቅ በችሎታውም በጠባዩም ልክ እንደ መልኩ የጠራ ነው። ለእሱ ሽምግልና በመመረጣችንም ክብር ይሰማናል። |

የሴት ቡድን - መልካም! ጥያቄያችሁ ተገቢም የተለመደም ነው፡፡ ግን አሁኑኑ አዎ ብለን ልንሸኛችሁ አንችልም፡፡ ስለ ልጅየው መተዳደሪያ፥ ጠባይና አጠቃላይ ሁኔታ ልጃችንንም ፈቃዷንና አዎንታዋን እንጠይቃለን፤ ዘመድ አዝማድም እናማክራለን፡፡ ስለዚህ አንድ ቀጠሮ ሰጥተን ለዛሬው እንሸኛችኋለን፡፡

የወንድ ወገን - እሺ! እግዜር ያክብርልን! ቀጠሮውን ቀን እንድትቆርጡልን በትህትና እንጠይቃለን፡፡ አባትና እናት በመመካከር የዛሬ ሳምንት እሁድ በአምስት ሰዓት አካባቢ ሊመጡ ይችላሉ (ጠያቂውም ተጠያቂውም ሽማግሌዎች ፈገግታ ይታይባቸዋል፥ቀጠሮ መሰጠቱ ራሱ ከመስጠት ይቆጠራልና፡፡) ከዚያም የወንድ ቡድን ሽማግሌዎች በሁኔታው እየተደሰቱ ይመለሳሉ፤ የተባለውንም ለወንዱ ቤተሰብ ወይም ላግቢው ይነግራሉ፡፡ በቀጠሮውም ቀን ተመልሰው በተባለው ሰዓት ይደርሳሉ፡፡

የወንድ ቡድን - አሁንም በሴቷ ቡድን ሽማግሌዎች ፊት በመቆም " ለዚህ ቀን ቀጠሮ ሰጥታችሁን በደስታ ተመልሰን ሄደናል፥ ዛሬ የመጣነው ደግሞ መልስ ለመስማት ነው፡፡"

የሴት ቡድን - ጉዳያችሁ ላይ ተነጋግረናል፡፡ ልጃችንንም ሌላ ቤተሰብ አነጋግረን ጉዳዩን አጣርተን ተቀብለናል፡፡ ጋብቻውም እንዲፈጸም ፈቅደናል፡፡

የወንድ ቡድን - ሁሉም በደስታ እጅ በመንሳት ፈገግታ ያሳያሉ፡፡ "በጣም እናመሰግናለን ለሰጣችሁን አክብሮት ክብርና ምስጋና ለእናንተ ይሁን፡፡" ብለው ለመሄድ እጅ ይነሳሉ፡፡

የሴት ቡድን - ቁጭ በሉ፥ ተቀመጡ፡፡ ( ወዲያውኑ ለመቀላቀላቸውና ለመስማማታቸው) ምልክት የምግብና የመጠጥ ግብዣ ያደርጋሉ፡፡

**በመጨረሻም፥**

የወንድ ቡድን - እንግዲህ ሁለቱ ተጋቢዎች ከቤተሰቦቻቸው ጋር ተነጋግረው የጋብቻውን ቀን እንዲወስኑ ፈቃዳችሁን እንጠይቃለን፡፡ በመጨረሻም ይሰነባበታሉ፡፡